ታህሣሥ 27 ቀን 1998 ዓ.ም

የሰበር መ/ቁ. 10797

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ አሰግድ ጋሻው
4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ - ጠበቃ ተሾመ ገ/ማርያም ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም - ቀርበዋል
2. አቶ ሁሴን አብደላ - አልቀረበም
3. አቶ ንጉሴ ኃይሉ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለበት በማለት ሥህተቱ በዚህ ችሎት ታይቶ እንዲታረም ባመለከቱት መሠረት ነው፡፡

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ቁጥር 1/89 በሆነ የወንጀል መዝገብ መጋቢት 5 ቀን 1992 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪዎቹ ለአመልካች በጠቅላላው 16,000.000 /አስራ ስድስት ሚሊዮን/ የአሜሪካን ላር እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የአመልካች ጠበቃ ይህንኑ ውሣኔ መሠረት በማድረግ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 መሠረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ የተባለውን ብር ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲታዘዝለት አመልክቷል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ በሁለቱም ወገኖች በኩል ያሉትን ባለጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች በጉዳዩ ያገባናል የሚሉትን ወገኖች አከራክሮ ካበቃ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት አፈፃፀም የሚጠየቅበት ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የበኩሉን ውሣኔ አሳልፏል፡፡ ለውሣኔውም መሠረት ካደረጋቸው ምክንያቶች መካከል፤ በአጠቃላይ ክሱ የሚያተኩረው ተፈፀመ በተባለ የወንጀል ጉዳይ ላይ እንጂ የፍትሐብሔር ይዘት እንደሌለው፣ የክሱ አቅራቢና ባለቤት ዐቃቤ ሕግ ሲሆን ጠሪዎቹ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሣሽ ሆነው የተወሰነባቸው ከመሆኑ ውጪ ከአመልካቹ ጋር በገንዘብ ክርክር እንዳልነበራቸው እና ሌሎች ነጥቦችንም በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ስለ ገንዘቡ ጉዳይ ሊነሣ የቻለው ከመወረስ ሁኔታ ጋር በማያያዝ የግል ተበዳዩን መብት ለመጠበቅ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት የሚፈፀም አይነት ፍርድ ለመስጠት እንዳልሆነ መረዳት እንደሚቻል ገልጾ የቀረበው የአፈፃፀም ጥያቄ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

አቤቱታው ለሠበር ችሎት የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው አመልካችም በአቤቱታው፣ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ከመሠረታዊ ፍርዱ ዓላማ እና ግብ የራቀ፣ የሕግ ግድፈት የሚታይበት እንዲሁም የአመልካችን ሕጋዊ መብት ገፍፎ በፍርድ የተወሰነለትን መብት እንዲያጣ ያደረገ መሆኑን ገልጾ ውሣኔው ውድቅ እንዲደረግለት፤ በአንፃሩ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ.ቁ.1/89 የአሁኖቹ ተጠሪዎች ለአመልካች የተጠቀሰውን 16,000.000 የአሜሪካን ላር እንዲመለስ በወንጀሉ ጉዳይ



አጣምሮ የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 መሠረት እንዲፈፀምለት አመልክቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረባቸው መልስ በአጭሩ፣ አመልካቹ በወ.መ.ሕ.ቁ. 100 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 154 መሠረት በተጠሪዎቹ ላይ በግል ተበዳይነት የፍትሐብሔር ክስ አለማቅረባቸውን፣ የፍ/ብሔር ክስ በጣምራ እንዲታይ አቤቱታ ባልቀረበበት የወንጀል ክስ የሚሰጥ ውሣኔ ደግሞ ቅጣት እንጂ የካሣ ውሣኔ ሊሆን እንደማይችል እንዲሁም አመልካቹ መብት አጉናፅፎኛል የሚሉት ፍርድ ከአፈፃፀም አቤቱታው ጋር ተያይዞ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲደርስ አለመደረጉን ገልፃ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግላት አመልክታለች፡፡

2ኛ ተጠሪ ሁሴን አብደላ የጠ/ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት በሌለበት የወሰነበት ስለሆነ በዚህም ችሎት አልተገኘም፡፡ 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከ1ኛ ተጠሪ መልስ በተለየ ሁኔታ፣ የወንጀል ችሎቱ ስለ አመልካቹ ገንዘብ ሊያነሣ የቻለው ገንዘቡ በመንግሥት እንዳይወረስ ከማሰብ ጋር አያይዞ መሆኑን የፍትሐብሔር ይግባኙን የመረመረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁ. 1/89 ላይ የተሰጠው ውሣኔ መንግሥት በተጠሪዎች ላይ የሚጠይቀውን የፍ/ብሔር ጉዳይ እንደማያጠቃልል ተገልጾ እያለ በዚህ ተመሣሣይ የወንጀል መዝገብ ውሣኔ በጉዳዩ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያላነሣን ወገን የፍ/ብሔር ጉዳይ ጭምር ያካተተ ነው ለማለት እንማያስደፍር፤ በሌላ በኩል የሰበሩ አቤቱታ ከቀረበበት አፈፃፀም ክርክርና ትእዛዝ በኋላ አመልካች በስዊዘርላንድ የፌዴራል ፍ/ቤት አስወስነው ገንዘባቸውን ወስደው ሳለ በድጋሚ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው አግባብ እንዳልሆነ ገልጾ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ጠበቃ በመልስ መልሱ አቤቱታውን አጠናክሮ የተጠሪዎችን መልስ ተችቷል፡፡ በበኩላችን መዝገቡን መርምረናል፡፡ ምላሽ ማግዕት የሚገባው ሆኖ ያገኘነው ነጥብ፣ በዚህ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት አፈፃፀም ሊጠየቅበት የሚችል ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡

ለዚህ ጉዳይ መነሻ በሆነው የወንጀል መዝገብ ቁ.1/89 የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት መጋቢት 5 ቀን 1992 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ለአመልካች መመለስ የሚገባቸውን 16,000.000 (አስራ ስድስት ሚሊዮን) የአሜሪካን ላር እንዲከፍሉ ፈርዷል፡፡

ክሱ የሚያተኩረው ተፈፀመ በተባለ የወንጀል ጉዳይ ላይ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የወንጀል ክሱን የመረመረውና የወሰነው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ መሆኑን፣ ከእነዚህ አንዱ ወንጀሉን ፈጽመዋል በተባሉት ሠዎች ላይ የእሥራትና የገንዘብ መቀጮ መወሰን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተጠሪዎች ከአመልካችና ከመንግሥት ወሰዱ የተባለውን ገንዘብ ለባለቤቶቹ እንዲመለሱ መፍረድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አሁን የተጠየቀው ገንዘብ የአመልካች ገንዘብ ስለመሆኑ መረጋገጡን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

እንደሚታወቀው ማናቸውም ሕግ ተላላፊ በወንጀል ሥራው ያገኛቸው ገንዘብና እቃዎች ሕጋዊ ባለንብረቱ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ሊመለሱለት እንደሚገባ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ.99(2)ዬ ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶችጦ በሚለው ክፍል የደነገገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ/ቁ. 1/89 አሁን የተጠየቀውን ገንዘብ ለባለቤቱ ሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እንዲመለስ ውሣኔ የሰጠውም ይህንኑ ሕግ መሠረት አድርጐ እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ባለንበረቱ ገንዘቡን ወይም ንብረቱን ለመረከብ አዲስ ክስና ክርክር መመስረት ሳያስፈልገው በቀጥታ መረከብ እንደሚችል ነው፡፡ አሁን የተነሳው የአፈፃፀም ጥያቄም ይህንኑ ውሣኔ መሠረት አድርጐ ተጠሪዎቹ ከላይ ተጠቀሰውን ገንዘብ እያንዳንዳቸው በየድርሻቸው መመለስ የሚገባቸውን ያህል እንዲከፍሉ እንዲታዘዝ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ የአፈፃፀም ጥያቄ ክፍ ሲል በጠቀስነው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ አኳያ የገንዘቡ ወይም የንብረቱ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ከመሆኑ ውጭ ባለሀብቱ የፍትሐብሔር ክስ አላቀረበም ወይም ፍርድ ያገኘበት ውሣኔ ለአፈፃፀም የሚያበቃ የፍትሐብሔር ፍርድ አይደለም ተብሎ ሊከለከል የሚችል አይደለም፡፡



ለማጠቃለል ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በፍርድ የተወሰነውን ገንዘብ የውሣኔው ባለመብት ሌላ ቀጥታ የፍትሐብሔር ክስ ማቅረብ ሣያስፈልገው በቀጥታ ሊፈፅም የሚቻል ፍርድ ነው በማለት ይህን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ/ቁ. 1/89 ስለገንዘቡ አመላለስ አስመልክቶ በሰጠው ውሣኔ የአሁኑ አመልካች በፍርዱ ውሣኔ በተሰጠው ምርጫ መሠረት ገንዘቡን ለማስመለስ በበኩሉ ያቀረበውን ጥያቄ መርምረን በሚከተለው መልኩ እንዲፈፀም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. 1ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ ወ/ሮ ሸዲያ ናዲም የአሜሪካ ላር 9,000.000 (ዘጠኝ ሚሊዮን ላር)፤
2. 2ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለዕዳ አቶ ሁሴን አብደላ የአሜሪካን ላር 6,443.447.95 (ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሦስት ሺ አራት መቶ አርባ ሰባት ላር ከዘጠና አምስት ሣንቲም)
3. 3ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ አቶ ንጉሤ ኃይሉ የአሜሪካን ላር 556,324.05 (አምስት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺ ሦስት መቶ ሃያ አራት ላር ከዜሮ አምስት ሣንቲም) በጠቅላላ 16,000.000 (አሥራ ስድስት ሚሊዮን የአሜሪካን ላር) ለፍርድ ባለመብቱ ለአሁኑ አመልካች ለሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እንዲመልሱ ታዟል፡፡

- በወ.መ.ቁ. 1/89 ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት መንግሥት ከ1ኛ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ ከወ/ሮ ሻዲያ ናዲም ላይ የሚፈልገውን ገንዘብ ከሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ አስቀድሞ እንዲወስድ ታዟል፡፡
- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ.5915 ህዳር 12 ቀን 1995 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡